# ስለ ሲያትል የቆሻሻ ማከማቻና የአረም እና የሜዳ አዝርዕት ደንቦች አጭር መምሪያ

## ታላላቅ ተጎራባች የንግድ ዲስትሪክቶች

የሲያትል ከተማ በደቡብ ምሥራቅ ሲያትል የሚኖሩና የሚሠሩ ሰዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የልማት ተግባር በማከናወን እና በማበረታታት ላይ ናት፡፡ የከተማይቱ እንቅስቃሴዎች በደቡብ ምሥራቅ ሲያትል የእንቅስቃሴ አጀንዳ፡ በጉርብትና ዕቅዶች እንዲሁም በሊንክ ላይት ሬይል የጣቢያ አካባቢ ዕቅዶች አማካኝነት በማኅበረሰቡ እየተገለጹ ናቸው፡፡

ከተማይቱ በደቡብ ምሥራቅ ሲያትል በምታከናውነው የልማት ተግባር እንደ አንዱ ክፍል ሆኖ፡ የንግድ ሥራ ባለቤቶች ስለ ቆሻሻ ክምችትና ከመጠን በላይ ያደጉ ተክሎች አወጋገድ ደንቦች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለመርዳት ቆርጣ ተነስታለች፡፡ እነዚህ ደምቦች የታላላቅ ተጎራባች የንግድ ዲስትሪክቶችን ደኅንነት በመጠበቅና ውበት እንዲኖራቸው በማድረግ ይደግፏቸዋል፡፡

### የንግድ ድርጅቶች የሚጠቀሙት እንዴት ነው?

የተጠራቀሙ ቆሻሻዎችን እና ከመጠን በላይ ያደጉ የሜዳ አዝርዕት ማስወገድን የሚጠይቁት ደንቦች በባሕሪያቸው በውበት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ አይደሉም፡፡ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ንጽሕናቸው የተጠበቀ በመሆኑ የተነሳ አካባቢያዊ የንግድ ድርጅቶች በሚከተለው ሁኔታ ቀጥተኛ ጥቅሞችን ያገኛሉ፡፡

- ተጨማሪ ደምበኞችን በመሳብ
- የንግድ ድርጅቶችን የገንዘብ አቅም በማሳደግ
- አዳዲስ የንግድ ድርጅቶችን በመጋበዝ የንግድ ዲስትሪክቱን በማጠናከር
- ደኅንነታቸው ይበልጥ የተጠበቀ ጤናማ አካባቢዎችን በመፍጠር

### የቆሻሻ ማከማቻ ምንድን ነው?

የቆሻሻ ማከማቻዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- መሠረታዊ የቆሻሻና የውድቅዳቂ ነገሮች ከረጢቶች
- አሮጌ የቤት ዕቃዎችና መሣሪያዎች
- አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎች
- ሳንቃዎችን እና ቀለሞችን ጨምሮ እንደገና አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ዕቃዎች

### አረምን እና የሜዳ አዘርዕትን የሚመለከቱ የደምብ መጣሶች ምንድን ናቸው?

ከልክ በላይ ያደጉ አረሞች እና የሜዳ አዝርዕት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከፈጠሩ የከተማቱን ደምብ ይጥሳሉ፡፡

- በእግረኛ እና በእያንዳንዱ ቤት መግቢያ መንገዶች ላይ ከመጠን በላይ ያደጉ አዝርዕቶች
- ከመጠን በላይ ያደጉ አዝርዕቶች በእግረኛና በተሽከርካሪ መንገዶች ላይ በቂ እይታ የማይኖርበት አኳኋን ሲፈጥሩ
- የትራፊክ ምልክቶችን ሲሸፍኑ

### የቆሻሻ ማከማቻ ሁናቴዎችን ያስወግዱ





የማይፈለጉ መኪናዎች እና የቆሻሻ ማከማቻ የደምበኞችን ስሜት ሊያዳክሙ ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ ያልሆኑ ዕቃዎችን በማስወገድ ለደምበኞች ተስማሚ የሆነ አካባቢን ይፍጠሩ፡፡

የሲያትል ከተማ
የእቅድ እና የልማት ክፍል

## ደምቦችን እንዴት ለማክበር እችላለሁ?

የሲያትልን የቆሻሻ ማከማቻን እና የአረም እና የሜዳ አዝርዕትን ደምቦችን መከተል የማይንቀሳቀስ ንብረትን በንጽሕና በመያዝ እና በማደስ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ከቤትዎ ውጭ መጋዘን መዘጋጀትን ለማሰወገድ፡ አስፈላጊ ያልሆኑ ዕቃዎችን ያስወግዱ፡፡ ሕዝቡ ጎዳናዎችን፡ የእግረኛ መንገዶችንና ወደ ቤት መግቢያ መንገዶች በቀላሉ ለመጠቀም ይችል ዘንድ አረም እና የሜዳ አዝርዕትን በአግባቡ ይቆጣጠሩ፡፡

<u>እነዚህን ደንቦች ስታስፈጽም የከተማይቱ ግብ የሕጎችን መከበር እንጂ ቅጣት አይደለም፡፡</u> የሲያትል ከተማ የሕግ አከባበር ሂደት ከተማይቱ ከንግድ ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንድትሠራ ያስችላታል፡፡

አንዳንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤቶች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ራሳቸው ለመፍታት እንደሚያስቸግራቸው ከተማይቱ ታውቃለች፡፡ በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሁናቴዎች ውስጥ ከተማይቱ ምንም ዓይነት አማራጭ ለሌላቸው ወይም ደንብ መተላለፍን ለማረም እርዳታ ከሚሹ ግለሰቦች ጋር አብራ የምትሠራ ሲሆን፡ ይህም የውጭ የማማከር አገልግሎትን እና/ወይም የጽዳት አገልግሎቶችን ሊጨምር ይችላል፡፡

የንግድ ድርጅቶች እነዚህን ደምቦች አክብረው መፈጸማቸው በቀን እስከ 500 ዶላር የሚደርስ ቅጣትን ከመቀጣት

### አረሞችን እና የሜዳ አዝርዕትን ይቆጣጠሩ





ከመጠን በላይ ያደጉ አረሞች እና የሜዳ አዝርዕት የእግረኛ መንገዶች በደምበኞችና በሕዝቡ ዘንድ ማራኪ እንዳይሆኑ ያደርጋሉ፡፡

**በእርስዎ ርዳታ ታላላቅ ተጎራባች የንግድ ዲስትሪክቶችን መፍጠር እንችላለን፡፡**

### በከተማይቱ የደምብ አከባበር ሕጎች ላይ ለውጦች እንዲደረጉ ስለ ቀረቡ ሃሳቦች የበለጠ መረጃን ለማግኘት፡

ድረገጽ፡ www.seattle.gov/DPD/Enforcement/Clean_Up_Your_Act/Overview/default.asp

የሕግ ማስፈጸሚያ መረጃ፡ (206) 615-0808

### ሕግን አክብሮ ሰለመፈጸም ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት

ድረገጽ፡ www.seattle.gov/dpd/enforcement/code_compliance/Overview/